NATIONAL CENTER ON
Early Childhood Health and Wellness

# የጤንነት ትምህርት፡ የጤና መረጃዎችን ለመረዳት እና ለመጠቀም ዋናው ቁልፍ ነገር

በቅድመ ህፃንነት የጤና እና ደህንነት ጉዳይ ላይ ከብሄራዊ ማዕከል ለወላጆች የተሰጠ ጠቃሚ መረጃ

## ሐኪምዎ የሚነግርዎትን ነገር መረዳት

የጤና ትምህርት ማለት የጤና መረጃን የሚረዱበት እና ስለ ጤና እና የህክምና ክብካቤ ጥሩ ምርጫ ለማድረግ የሚችሉበት ነው።

### አስፈላጊነቱ ምንድን ነው?

አብዛኛዎቹ ሰዎች ለራሳቸው እና ለቤተሰባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ የሚያስፈልጋቸውን የጤና መረጃ በቀላሉ መረዳት አይችሉም።

### ቤተሰቦች ወይም የህጻናት እንክብካቤ ሰጪዎች የጤና መረጃዎችን መረዳት እንዲሁም በእንዴት አይነት ሁኔታ መጠቀም እንዳለባቸው ማወቅ ሲችሉ፤ ህጻናት በአብዛኛው

- ጥቂት የትምህርት ቀናትን ሊያመልጣቸው ይችላል።
- አስፈላጊ ሳይሆን ወደ የህክምና ባለሙያው መሄድ ወይም ድንገተኛ ክፍል መጎብኘት እምብዛም አይኖርም።
- ጤናማ ህይወት ይኑሩ
- የመከላከያ ጥንቃቄዎችን ለምሳሌ የጉንፋን ክትባቶችን ይውሰዱ።
- ጥቂት አደጋ የሚከሰትበት ከአደጋ የተጠበቀ ቤት ውስጥ ይኑሩ።

### የጤና መረጃዎችን መጠቀምና ለመገንዘብ የሚረዱ መንገዶች ጠቀሜታቸው፤

- ከዶክተሩ ጋር ማውራት
- ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የሀኪሙን መመሪያዎች መከተል
- መድሃኒቶችን በትክክለኛው መንገድ መውሰድና መስጠት
- የህክምና ምርመራና ጥንቃቄ በአግባቡ ለማግኘት
- ልጅዎ ሲታመም ምን ማድረግ እንዳለብዎት ለማወቅ
- እንደ ስኳር፣ አስምና ካንሰር ያሉ በሽታዎችን በቅድሚያ ለመከላከል
- ለእርስዎና ለቤተሰብዎ ጤናማ ውሳኔ ለመወሰን
- እርዳታ ለመጠየቅ

## ልጅዎን ለመርዳት ማድረግ ያለብዎት ተግባራት

- የጤና መረጃ ቅጹን በአግባቡ ካልተደረዱት እና እንዴት መሙላት እንዳለብዎ ካላወቁ እርዳታ ይጠይቁ።
- የሚቀርብልዎት ቅጽ እርስዎ ለማንበብ ቀላል በሆነልዎት ቋንቋ እንዲሆንልዎት ይጠይቁ።
- ከዚህ በፊት የነበረዎትን ጥያቄዎች ይጻፉ እና በማንኛውም የጤና ምርመራ ጉብኝትዎ ጊዜ ይዘው ይቅረቡ።
- ሀኪሙ/ሟ የሚናገረው/የምትናገረው ካልገባዎት እንዳልተረዱት ይንገሩ።
- Gወደ ቤተ መጻህፍት በመሄድ ስለ መድሃኒትና ስለጤና ጉዳዮች የተመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ይሞክሩ።
- እርስዎን የሚመለከት የጤና ጉዳይን በተመለከተ ከዋናው መስሪያ ቤት ወይም ከህጻናት እንክብካቤ መርሃ ግብር መረጃ ለማግኘት ይጠይቁ።
- በአካባቢው በሚገኘው ማህበረሰብ ወይም በልጆችዎ የሄድ ስታርት መርሃ ግብሮች ወርክ ሾፖች ላይ ይካፈሉ።

